የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት

ስለመቋቋሙ የተሰጠ መግለጫ

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር የበላይ ጠባቂ በመሆናቸው የግርማዊነታቸው አጽም ተፈልጎ እንዲወጣና በክብር እንዲያርፍ ማኅበሩ በወቅቱ ለነበረው የኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ጥያቄ አቅርቧል:: በዚሁ ጥያቄ መነሻና የሽግግር መንግሥቱም ባደረገው ትብብርና ጥረት የግርማዊነታቸው አጽም ለሁለት ቀን ከተፈለገ በኋላ ከተሰወረበት አልባሌ ቦታ የካቲት 8 ቀን 1984 ዓ.ም. በጥንቃቄ ሊወጣ ችሏል:: እነዚህም ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ የታወቁ ናቸው::

የታላቁ ንጉሠ ነገሥት አጽም እንደተገኘም አጽሙን በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለማሣረፍ ፕሮግራም እንዲያዘጋጅ አንድ ኮሚቴ ተሰየመ:: ~~ፕሮግራሙን እንዲያዘጋጅ~~ የተሰየመው ኮሚቴ የፕሮግራም ዝግጅቱን በማጣደፍ ላይ እንዳለ የሕዝብ ተወካዮች ቀርበው "የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ አጽም በክብር ማረፍ ስለሚገባው ለዝግጅቱ በቂ ጊዜ እንዲገኝ በጊዜያዊነት ቤታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም እንዲያርፍ ይደረግ" የሚል ጥያቄ አቀረቡ:: ንጉሣዊ ቤተሰቦችም በዚህ ሃሳብ በመስማማታቸው፣ ከአርበኞች ማህበር በተጻፈ ደብዳቤ አማካይነት የግርማዊነታቸው አጽም ቤታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም ገዳም በአደራ እንዲያርፍ ከተደረገ አራት ዓመት አልፎታል::

አረመኔው ደርግ በግፍ እየገደለ በየአልባሌ ወረዳ ሥፍራ የጣላቸው የኢትዮጵያውያን አጽም በኢትዮጵያ ሽግግር መንግሥት ፈቃድ እየተፈለገና እየተሰበሰበ በክብር እንዲያርፍና እንደየአስፈላጊነቱም መታሰቢያ እንዲሠራለት ተደርጓል:: የግርማዊነታቸውም አጽም ከፖለቲካ ውጭ በሆነ መልክ በክብር እንዲያርፍ በመንግሥት የተፈቀደ ቢሆንም፣ አሁንም በጊዜያዊነት በአደራ ከተቀመጠበት ታዕካ ነገሥት በዓታ ለማሪያም ገዳም ይገኛል::

ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ በረጅሙ የመሪነት ዘመናቸው ለኢትዮጵያ ዕድገት ያደረጉት አስተዋጽዖ ወደፊት በሰፊው ይገለጻል:: ሆኖም፣ በተለይ የኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር፣ ታሪኳም በዓለም ጎልቶ እንዲታወቅ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ማህበራዊ ኑሮ እንዲዳብር፣ በትምህርትና በዕውቀት እንዲያድግ አጅግ የጣሩ መሆናቸው የታወቀ መሆኑ እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይገባል:: ጥረታቸውም የተሳካ መሆኑ ግልጽ ነው::

እንዲሁም በአገሪቱ ላይ ከውጭ ከባድ ፈተና በደረሰባት ጊዜ ሁሉ በጦር ሜዳውም ሆነ በፖለቲካው ያሳዩት ተጋድሎና ፍትሕ እንደሚያሸንፍ የነበራቸው የእምነት ጽናት ለኢትዮጵያ የዓለምን ሕዝብ አድናቆት አትርፎላታል::

ግርማዊነታቸው ለአፍሪካ አንድነት፣ ነጻነትና ሰላም በመታገል ከፍተኛ ውጤት ያስገኙ ናቸው::

የኢትዮጵያ ታላቅ መሪና የአፍሪካ አባት የነበሩት ንጉሠ ነገሥት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፣ ለአፍሪካና ለዓለም ጭምር ለፈጸሙት የመሪነት አገልግሎትና የሽምግልና ድርሻ ቋሚ መታሰቢያ ማቆየት ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠበቅና የተቀደሰ ተግባር ነው:: ባልተሟላ አደረጃጀት አጽማቸው ወደ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እንዳይዛወር የሕዝብ ተወካዮች በመጀመሪያውም የተቃወሙት በዚሁ መሠረት ነው::

የግርማዊነታቸው አጽም ተገቢው ክብርና ሥነስርዓት ተደርጎለት ባለማረፉ፡ ባለፉት አራት ዓመታት የግርማዊነታቸው ባለውለታ ከሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብና ሥራቸውን አድናቂ ከሆኑት ሀቀኛ የውጭ አገር ታላላቅ ሰዎች የቅሬታ፣ የሀዘንና የስሞታ ድምጽ ተሰምቷል:: በፍትሕና ርትዕ የሚያምኑትን ኢትዮጵያውያን ሕሊናም ዕረፍት የሚነሳ ሆኖ ቆይቷል:: ከዚህ የታሪክ ትዝብትና ዘላለም ፀፀት ለመዳን አጽሙን ንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት በነበሩበት ዘመን እንዲዘጋጅ ባደረጉበት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሚገኘው መካነ መቃብር በክብር ማሳረፍና ተገቢው መታሰቢያም እንዲቋቋምላቸው ማድረግ ዓቢይና ወቅታዊ ተግባር መሆኑ ግልጽ ነው::

ይህን ክቡር ዓላማ ከግብ ለማድረስ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው ውይይት ካደረጉ በኋላ፣ የንጉሣዊ ቤተሰብ፣ የሕዝብና የአርበኞች ማህበር ተወካዮች አባል የሆኑበት "የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት" [illegible] አቋቁመዋል:: ድርጅቱም በሕግ እንዲታወቅላቸው ለተገቢው መንግሥት መሥሪያ ቤት የድርጅቱን መመሥረቻ ሰነድ በማያያዝ አቅርበዋል::

ይህ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ድርጅት በኢትዮጵያም ሆነ በውጭ ፍትሕና ርትዕ ወዳጅ ከሆነ ወገን ሁሉ ገንቢ ሃሳብና እንዲሁም የንብረትና ገንዘብ ሰፊ ድጋፍ እንደሚያገኝ አንጠራጠርም:: አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንና የግርማዊነታቸው ወዳጅ የሆኑ የውጭ አገር ሰዎች ሁሉ በዚህ መግለጫ አማካይነት የድርጅቱን መቋቋም እንደተረዱት ተስፋ እናደርጋለን::

የተቋቋመው የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት በአሁኑ ወቅት 27 አባላት በሚገኙበት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመራ ሲሆን፣ በሥሩም ሰባት የቴክኒክ ኮሚቴዎች አዋቅሮ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል:: ስለሕዝብ ተሳትፎ፣ አባላት አመዘጋገብና መዋጮ አከፋፈል፣ እንዲሁም ወደፊት ስለሚደረገው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለሕዝብ መግለጫ የሚሰጥ ሲሆን፣ የማንኛውም መገናኛ ብዙሃን ወኪሎች ለሚጠይቁት ማብራሪያ በራችን ክፍት እንደሚሆን እናረጋግጣለን::

ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት
የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ
መታሰቢያ ድርጅት
የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት
መመሥረቻ ሠነድ

መግቢያ

«ፍትህ ርትዕ የተለየው ሠላም ዘላቂነት የለውም...» በ1984 ዓ.ም. በየካቲት 8 ቀን በዕለተ እሁድ በጊዜው የሽግግር መንግሥት መልካም ፈቃድና ተባባሪነት በጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር አሳሳቢነት የግርማዊ ቀደማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ አስከሬን በወታደራዊ ደርግ የአረመኔነት ድርጊት ከተደበቀበት የውርደት ሥፍራ በብዙ ጥንቃቄ እና ጥረት ተቆፍሮ ወጥቶ ለቤተሰባቸው ከተሰጠ በኋላ በጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር አማካይነት በታዕካ ነገሥት ባዕታ ገዳም በጊዜአዊነት በአደራ እንዲቆይ የተደረገ መሆኑ ስለሚታወቅና ወደፊት ወደራሱ የክብር ሥፍራ ተዛውሮ የሚያርፍ መሆኑ ስለሚታመን፤

ፋሽስቱ ወታደራዊ ደርግ በግፍ እየገደለ አጽማቸው እንኳ እንዳይገኝ አሳቻ ሥፍራ ደብቆ የቀበራቸው ኢትዮጵያውያን አጽም በጊዜው የሽግግር መንግሥት ትብብር እና ጥረት ተቆፍሮ እየወጣ በክብር ቦታ እንዲያርፍና እንደየሁኔታው መታሠቢያ እንዲሠራለት ሲደረግ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ አጽም ወደክብር ቦታው ተዛውሮ ሳያርፍ በጊዜአዊነት እንዲቆይ በተደረገበት ሥፍራ እስካሁን መገኘቱ ስለሚታወቅ፤

የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ አጽም በህይወት ሳሉ በተሰራው በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በሚገኘው መካነ መቃብራቸው እንዲያርፍ እና ተገቢ የክብር ቦታውን እንዲያገኝ ማድረግ የሚገባ መሆኑን ስለአመን፤

እንዲሁም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ በረጅሙ የመሪነት ዘመናቸው የኢትዮጵያ ነፃነትና አንድነት ተጠብቆ እንዲኖር ታሪኳም በዓለም ጉልቶ እንዲታወቅ በመጣራቸው የኢትጵያ ሕዝብ ማኅበራዊ ኑሮ እንዲዳብር በትምህርትና በእውቀት እንዲያድግ በማድረጋቸው፤

ለአፍሪካ አንድነት፣ ነፃነትና ሠላም በመታገል ከፍተኛ ውጤት በማስገኘታቸው፣ ኢትዮጵያ በዓለም ሠላም ማስፈን ተግባሮች ተካፋይ እንድትሆን በማድረግ አጥጋቢ ውጤት እንድታገኝና አኩሪ ታሪክ እንድታተርፍ በመታገላቸው፤

በታላቁ ንጉሠ ነገሥት ላይ ፋሽስት ደርግ በፈጸማቸው እኩይ ተግባሮች አረመኔነቱ የተጋለጠ ቢሆንም ያረከሰውን የኢትዮጵያን ህዝብ ፍትህ ርትዕ ወዳድነቱን ታሪክ ማደስ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበን፣ ለግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መልካም ሥራዎች መታሰቢያዎችን ለማቋቋም፣

እኛ ስማችን በገጽ 9-10 ላይ የተመለከተው ሰዎች በዚህ መመሥረቻ ሰነድ «የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት»ን መሥርተናል::

አንቀጽ አንድ
መጠሪያ

ይህ ድርጅት «የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት» ተብሎ ይጠራል::

አንቀጽ ሁለት
<u>ትርጉም</u>

በዚህ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት መመሥረቻ ሠነድ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ያለው መሆኑን በግልጽ ካላመለከተ በስተቀር፤

2.1 «ጉባዔ» ወይም «ጠቅላላ ጉባዔ» ማለት በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ዓላማ እና ተግባር አምነውና ግዴታቸውን አሟልተው በድርጅቱ የአባላት መዝገብ የተመዘገቡ ሰዎች የሚያደርጉት ጠቅላላ ስብሰባ ነው::

2.2 «ድርጅት» ማለት በዚህ የመመሥረቻ ሠነድ የተቋቋመው የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ነው::

2.3 «ኮሚቴ» ማለት በግርማዊ የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ ነው::

2.4 «አባል/ላት» ማለት የቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ዓላማ አምኖና ግዴታውን አሟልቶ የተመዘገበ በድርጅቱ የሥራ ክፍል ተመድቦ የሚሠራ ወይም ተራ ማኅበርተኛ የሆነ ሰው/ዎች ነው/ናቸው::

2.5 «ግርማዊነታቸው» ማለት ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ማለት ነው::

2.6 «ሥራ አስኪያጅ» ማለት የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ጽ/ቤትን በበላይነት ሥራውን እያስተባበረ የሚያካሂድ እና የሚመራ ሰው ነው::

2.7 «መመሥረቻ ሠነድ» ማለት ይህ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት የተቋቋመበት ሕጋዊ ደንብ ነው::

አንቀጽ ሦስት
<u>ምሥረታ</u>

3.1 ይህ ድርጅት በዚህ መመሥረቻ ሰነድ በፍ/ብሔር ሕግ ቁጥር 404 እና 408/1 መሠረት የተቋቋመ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ነው::

3.2 ድርጅቱ በማናቸውም የፖለቲካ ተግባር ውስጥ ሳይገባ የብሔረሰብ፣ የጐሣ፣ የሃይማኖት የእምነትና የጾታ ልዩነት ሳያደርግ የተቋቋመበትን ዓላማ ብቻ ይፈጽማል፤ ያስፈጽማል::

አንቀጽ አራት
<u>አድራሻ</u>

ዋና መሥሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ከተማ ይሆናል:: እንደአስፈላጊነቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይቋቋማሉ::

አንቀጽ አምስት
<u>ድርጅቱ የሚኖርበት ዘመን</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ዘመን የተቋቋመ ነው::

አንቀጽ ስድስት
<u>ዓላማ</u>

6.1 የግርማዊነታቸውን አጽም በአደራ በጊዜያዊነት ከተቀመጠበት ታዕካ ነገሥት ባዕታ ገዳም ቀደም ብሎ ወደተዘጋጀው መንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መካነ ቀብራቸው አዛውሮ በክብር ማሳረፍ::

6.2 በስማቸው መታሰቢያቸውን ማቋቋም

አንቀጽ ሰባት
<u>የድርጅቱ መዋቅር</u>

ድርጅቱ የሚከተለው መዋቅር ይኖሩታል

7.1 ጠቅላላ ጉባዔ
7.2 ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
7.3 የድርጅቱ ጽሕፈት ቤት

አንቀጽ ስምንት
<u>የአባላት መብትና ግዴታ</u>

ድርጅቱ ሚከተሉት ሦስት ዓይነት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የክብር አባላት
ለ. የተወሰነ ጊዜ አባላት
ሐ. ቋሚ አባላት

8.1 የክብር አባላት

ለድርጅቱ የላቀ አገልግሎት በማበርከታቸው ወይም ከፍ ያለ የገንዘብ ወይም የንብረት ስጦታ በማድረጋቸው ወይም የድርጅቱ አባል መሆናቸው ለድርጅቱ ክብር ወይም ልዩ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑ ሲታወቅ የድምጽ መስጠት መብት ሳይኖራቸው የክብር አባል እንዲሆኑ በኰሚቴው ውሣኔ የተመረጡ ሰዎች ናቸው::

8.2 <u>የተወሰነ ጊዜ አባላት</u>

ለድርጅቱ አገልግሎት በማበርከታቸው ወይም የገንዘብ ወይም የንብረት ስጦታ በማድረጋቸው በአገልግሎታቸውና በስጦታቸው መጠን ለተወሰኑ ዓመታት የድምጽ መስጠት መብት ሳይኖራቸው የድርጅቱ አባል እንዲሆኑ በኰሚቴው የተፈቀደላቸው ሰዎች ናቸው::

8.3 <u>ቋሚ አባላት</u>

በድርጅቱ ዓላማ አምነው አባል ለመሆን የሚፈልጉና የመመዝገቢያ ግዴታቸውን አሟልተው በአባልነት መዝገብ ተመዝግበው የአባልነት ክፍያና ሌሎች መዋጮዎችን አጠናቀው በወቅቱ የከፈሉና ሌሎችንም የአባልነታዊ ግዴታቸውን ያሟሉ አባላት ናቸው::

8.4 የቋሚ አባላት መብት

8.4.1 በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ዓላማና ተግባር የሚያምንና የድርጅቱ አባል ለመሆን የሚፈልግ መብቱን በሕግ ያላጣ ሰው የድርጅቱ አባል ለመሆን ጥያቄ ማቅረብና የመመዝገቢያ ግዴታውን አሟልቶ አባል መሆን ይችላል::

8.4.2 የመመዝገቢያ ግዴታውን አሟልቶ በአባላት መዝገብ የተመዘገበ ዓመታዊ የአባልነትና ሌሎች ወቅታዊ መዋጮዎችን አጠናቅቆ የከፈለና ሌሎች የአባልነት ግዴታዎችን የፈጸመ አባል በጠቅላላው ጉባዔ ስብሰባ የመካፈል የመመረጥና የመምረጥ በጠቅላላው የአባልነት የጋራ ሥራ ክንውን ተካፋይ የመሆን ሙሉ መብት አለው::

8.5 የቋሚ አባላት ግዴታ

8.5.1 በግርማዊ በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ መታሰቢያ ድርጅት ዓላማ አምኖና ፈቅዶ የድርድቱ አባል የሆነና በአባልነት መዝገብ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው መመዝገቢያና ወቅታዊ የአባልነት ክፍያዎችን አጠናቆ መክፈል አለበት::

8.5.2 ማንኛውም ቋሚ አባል በዓመታዊና በተለይ በሚጠሩ በጠቅላላ ጉባዔና ሌሎች ልዩ ለዩ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት የመምረጥና የመመረጥ ተሳትፎ የማድረግና በሚፈለግበትና በሚመደብበት የሥራ ክፍል ላይ ሆኖ ማገልገል አለበት::

8.5.3 አንድ ቋሚ አባል በራሱ ጥያቄ ወይም በድርጅቱ ውሳኔ ከአባልነት ሲወጣ ለድርጅቱ የከፈላቸውን የዘመኑንም ሆነ ያለፉትን ማንኛውንም ክፍያዎች እንዲመለስለት መጠየቅ አይችልም::

8.6 ቂሚ አባል ስለመቀበልና ስለማስወገድ

8.6.1 አንድ አባል ለድርጅት ሥራ አፈፃፀም ጉጂ ይሆናል ተብሎ ሲገመትና ኰሚቴው ጉዳዩን መርምሮ ሲወስን ወይም ግዴታውን ያልተወጣ ሆኖ ሲገኝ ከድርጅቱ አባልነት ይወጣል::

8.6.2 የአባሉን መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ከድርጅቱ አባልነት የወጣበት ምክንያት ይፋ አይሆንም::

8.6.3 አዲስ አባሎችን ለማስገባት ወይም ለማስወገድ በፍትሐ ብሔር ቁጥር 439 /1/ እና /2/ መሠረት ይፈጸማል::

አንቀጽ ዘጠኝ
የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

9.1 የጠቅላላ ጉባዔ የድርድቱ የበላይ ባለሥልጣን ነው::

9.2 በመመሥረቻው ደንብ የተገለጹትን ዓላማዎች የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ የሥራ አስፈጻሚ ኰሚቴ አባላትን መርጦ ይሾማል ይሽራልም::

9.3 ለድርጅቱ ዕድገት መስፋፋትና መጠናከር ያመነበትን ተግባር እንዲውል መመሪያ ይሰጣል::

9.4 የድርጅቱን የሶስት ዓመት መመሪያ ባጀት ያጸድቃል::

9.5 የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚያቀርበውንና የኦዲተሮችን ራፖርት መርምሮ ይወስናል::

9.6 የድርጅቱን እቅዶች እየመረመረ ይፈቅዳል::

9.7 አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዮችን እያጠና የሚያቀርብለት ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል::

አንቀጽ አሥር
<u>የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አመሠራረት</u>

10.1 ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሀያ አንድ አባላት ይኖሩታል::

10.2 አባላቱ ከመካከላቸው ሰብሳቢያቸውን መርጠው ይሾማሉ፣ ይሽራሉም::

10.3 አባላቱ የሚመረጡት በታማኝነታቸው የድርጅቱ ደጋፊ በመሆናቸው በችሎታቸው ብቃትና በሰፊ የሥራ ልምዳቸው ነው::

10.4 የአባላቱ የሥራ ዘመን አራት ዓመት ይሆናል::

አንቀጽ አሥራ አንድ
<u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር</u>

11.1 ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባዔ ነው::

11.2 የድርጅቱን ዋና ሥራ አስኪያጅ መርጦ ይቀጥራል፣ ይቆጣጠራል፣ መመሪያ ይሰጣል፣ ከሥራ ያሰናብታል::

11.3 የጠቅላላውን ጉባዔ ውሣኔዎች በተግባር ይተረጉማል::

11.4 የድርድቱን መመሥረቻ ሠነድ ተግባራዊነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል::

11.5 የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ፕሮግራሞችንና እቅዶችን ያጠናል፣ በጠቅላላ ጉባዔ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል::

11.6 የግርማዊነታቸው አጽም ማሳረፍ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምበትን ፕሮግራም እንዲዘጋጅ በማድረግ እየተከታተለ ያስፈጽማል::

11.7 የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት በሚገባ በሥራ ላይ መዋሉንና በሥርዓት መያዙን ይቆጣጠራል::

11.8 ለድርጅቱ ዓላማ ማስፈጸሚያ:-

- የአባላት መዋጮን ያሰባስባል::
- በአገር ውስጥና በውጭ አህጉራት ከሚገኙ የግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለሥላሴ ወዳጆች እርዳታና አስተዋጽኦ ይጠይቃል፤ ከው… ከስጦታ የሚገኘውንም ይሰበስባል::
- ከታሪክ ጋር የተያያዙ በዓላትን መነሻ በማድረግ [illegible] በማዘጋጀት ከቲኬቶች ሽያጭ፣ እንዲሁም ባጃጆች፣ [illegible] አጫጭር ትምህርታዊ ጽሑፎችን፣ በማዘጋጀትና በመሸ…

ገቢ እንዲያገኝ መመሪያ ይሰጣል::

11.9 በጠቅላላ ጉባዔው የጸደቀውን የሶስት ዓመት መመሪያ ባጀት መሠረት በማድረግ ለድርጅቱ ሥራ ማከናወኛ የሚያስፈልገውን ዓመታዊ ዝርዝር ባጀት ያጸድቃል፣ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል::

11.10 ዓላማውን ለማስፈጸም ገንዘብ ይበደራል፣ ውል ይዋዋላል::

11.11 የድርጅቱን ዓላማና ተግባር የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን እንደአስፈላጊነቱ ያቋቁማል፣ ሥራቸውን የሚያከናውኑበትንም ደንብና መመሪያ ያወጣል::

11.12 የድርጅቱን የባንክ ሒሳብ የሚያንቀሳቅሱ አባላት መርጦ ይወክላል::

11.13 የጐደሉ አባላት ሲኖሩ ኮሚቴው በድምጽ ብልጫ መርጦ ይመድባል፣ በጠቅላላውም ጉባዔ እንዲጸድቅ ያደርጋል::

11.14 የድርጅቱ የውስጥ ደንብ እንዲዘጋጅ ያደርጋል::

11.15 ሌሎች ሥራዎችንም እንደአጋጠመውና እንደቀረበለት ይፈጽማል::

አንቀጽ አስራ ሁለት
የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር

12.1 ተጠሪነቱ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው::

12.2 የኮሚቴው አባልና ፀሐፊ ሆኖ ይሠራል::

12.3 የጠቅላላው ጉባዔና የኮሚቴውን ውሳኔዎችና መመሪያዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን እየተከታተለና እየተቆጣጠረ ያስፈጽማል፣ ይፈጽማልም::

12.4 በሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ የተወሰኑ ጉዳዮችን በሚመለከቱ አግባብ ካላቸው መ/ቤቶች ድርጅቶችና ግለሰቦች ጋር ይገናኛል፣ ይፃፃፋል፣ በጉዳዮቹ ላይ ውሣኔ ይሰጣል:: ውሳኔውን ለኮሚቴው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል::

12.5 የግርማዊነታቸው አጽም ማሳረፍ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምበትን እቅድ ያዘጋጃል፣ የአፈፃፀም ፕሮግራም አውጥቶና በኮሚቴው አስወስኖ በሥራ እንዲተረጐም ይከታተላል::

12.6 የድርጅቱን ሥራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል::

12.7 መታሰቢያዎች የሚቋቋሙበትን ያቅዳል፣ በኮሚቴው እያስወሰነ እንዲደራጁ ያደርጋል::

12.8 አባላት እንዲበራከቱና አስተዋጽኦዋቸውም እንዲጐለብት ጥረትና ህ[illegible] ያደርጋል::

12.9 የድርጅቱን ዓላማና ተግባር ለበጐ አድራጊ ድርጅቶች ማኅበርተኞ[illegible] ግለሰቦ[illegible] በማስተዋወቅ ዕርዳታ የሚገኝበትን ዘዴ ይቀይሳል፣ ይከታተላል::

12.10 የድርጅቱ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሀብትና ንብረት በሚገባ በጥንቃቄ መያዙን ይቆጣጠራል::

12.11 የሥራ ማከናወኛ በጀት ተዘጋጅቶ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሣኔ እንዲቀርብ ያደርጋል፣ የተፈቀደውም በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል::

12.12 የገንዘብና የንብረት አስተዳደር በዘመናዊና ቀልጣፋ ዘዴ የሚመራበት የአያያዝና የቁጥጥር ሥርዓት አዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል::

12.13 ገንዘብ በወቅቱ ተሰብስቦ ባንክ እንዲገባና ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል::

12.14 ከሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ዋናው ሥራ አስኪያጅ የአስተዳደር፣ የሂሣብና የንብረት ኃላፊዎችን እንዲሁም የውስጥ ኦዲተርና ሌሎችንም ተፈላጊ የሰው ኃይል እንዲሟላ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል:: ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራቸውንም አዘጋጅቶ በተግባር ያውላል::

12.15 ለጠቅላላ ጉባዔ የሚቀርበው ሪፖርት በወቅቱ ተዘጋጅቶና በኮሚቴው ታይቶና ተወስኖ እንዲቀርብ ያደርጋል::

12.16 ድርጅቱን የሚመለከቱ ሌሎች ሥራዎችን እንደሁኔታው ያከናውናል::

አንቀጽ አሥራ ሦስት
የስብሰባ ሥነ ሥርዓት

13.1 ጠቅላላ ጉባዔ በሶስት ዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል:: ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ወይም ከቋሚ አባላት አንድ አምስተኛው ከጠየቁ በማንኛውም ጊዜ የጠቅላላውን ጉባዔ ስብሰባ መጥራት ይችላል::

13.2 የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ በዓመት አራት ጊዜ ይሰበሰባል:: አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም ከኮሚቴው አባላት አንድ አምስተኛው ከጠየቁ በማንኛውም ጊዜ የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ እንዲሰበሰብ መጥራት ይቻላል::

13.3 የጠቅላላው ጉባዔ ስብሰባ እንዲጠራ ከተወሰነበት ጊዜ ቢያንስ ከአሥራ አምስት ቀን የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ እንዲጠራ ከታሰበበት ከሰባት ቀን በፊት ስብሰባው የሚደረግበት ቦታ ቀንና ሰዓት በመግለጽ እንዲሁም የመነጋገሪያውን አጀንዳ በማያያዝ በአመችና አፋጣኝ ዘዴ ለአባልነት ጥሪ መላክ አለበት::

13.4 በጠቅላላ ጉባዔ ወቅት በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት ድምጽ ብልጫ ውሣኔ ይሰጣል::

13.5 የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ስብሰባ ምልዐተ ጉባዔ ከግማሽ በላይ ይሆናል:: ሆኖም ለአንድ ስብሰባ አባላት ሁለት ጊዜ ጥሪ ተደርጎላቸው ካልተገኙ በተገኙት አባላት ድምጽ ብልጫ ውሣኔ መስጠት ይቻላል::

13.6 በማናቸውም ስብሰባ ወቅት ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምጽ ብልጫ ይኖረዋል::

የድርጅቱ የገቢ ምንጭ

14.1 ከአባላት መዋጮ

14.2 ከግለሰቦች ድርጅቶችና አገሮች የሚገኝ እርዳታ

14.3 ከሌሎችም በንዑስ አንቀጽ 11.8 ከተጠቀሱት የገቢ ምንጮች የሆናል::

አንቀጽ አሥራ አምስት
የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት አያያዝ

በንዑስ አንቀጽ 11.2 ለሚመደበው ዋና ሥራ አስኪያጅ በአንቀጽ 12 በተዘረዘረው ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም በንዑስ አንቀጽ 11.11 እና 11.12 በተጠቀሰው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሥልጣን መሠረት በሚቋቋሙት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች አማካይነት የድርጅቱ ገንዘብና ንብረት በሚከተለው ሁኔታ ይያዛል::

15.1 የድርጅቱ ገቢ ገንዘብ በ48 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ባንክ ገቢ መሆን ንብረቱም በንብረት መዝገብ መመዝገብ አለበት::

15.2 ገንዘብና ንብረቱ በአስተማማኝና በሚገባ እንዲያዝ፣ እንዲጠበቅ፣ ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝና የንብረት አመዘጋገብና አጠባበቅ ሥነ ሥርዓት ይኖረዋል::

15.3 የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቱ በየዓመቱ ወይም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ይቆጠራል:: የንብረቱ ገቢ ወጭና ቀሪው ተመዛዝኖ ራፖር እንዲቀርብ ይደረጋል::

15.4 የበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን ያለው የአንድ ዓመት ጊዜ ይሆናል::

15.5 የበጀት ዓመቱ በአለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሳቡ ተጠናቅቆ መዘጋት አለበት::

15.6 የያንዳንዱ የበጀት ዓመት የገንዘብና የንብረት ገቢ ወጭና ከወጭ ቀሪ እንደዚሁም የንብረት አጠባበቅና አያያዝ የሥራው ክንውንና ኦዲት በውጭ ሕጋዊ ኦዲተሮች ተመርምሮ የተገኘው ውጤት ለ ጠቅላላ ጉባዔው መቅረብ አለበት::

አንቀጽ አሥራ ስድስት
የመመስረቻ ሰነድ ስለማሻሻልና የውስጥ ደንብ ማውጣት

16.1 ድርጅቱ ይኸን መመሥረቻ ሰነድ እንደአስፈላጊነቱ በጠቅላላ ጉባዔ በስብሰባ በሚገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ አሻሽሎ ሊሠራ ይችላል::